# የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና ፤ የሕብረት ጥያቄ

ከምንተስኖት ሲራክ

በብዙ አሁጉሮች እንደታየው ቅኝ አገዛዝም ሆነ ጸረ ሕዝብ ፤ ጸረ ዲሞክራሲ የሆኑ መንግሥታትን ለመታገል ወቅቱ በፈቀደ ሁኔታ የተለያዩ ቡድኖች ፤ ፓርቲዎች ፤ የኀበዝ አለቆች ፤ ካህናትና ሼኮች ከሊቅ እስከ ደቂቅ ተባብረው በመታገል ያገራቸውን ነፃነትና አንድነት የሕዝባቸውን ጥቅም ዕውን ለማድረግ ችለዋል ። ኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜያቶች የገጠማትን ወራሪዎች በተመሳሳይ ትብብርና ህብረት መመከት ብቻ ሳይሆን ባቸናፊነት ተወጥታ አንድነቷንም የበለጠ እያጠናከረች የመጣች አገር ናት ፤ በመሆኑም አያት ቅድመ አያቶቻችን ዛሬ ሀገሬ ብለን የምንኮራባትን ኢትዮጵያ አስረክበውን አልፈዋል ። ከውጪ ጠላትም በወረራት ወቅት በውስጧ የነበሩ የተለያዩ ነገሥታት እርስ በርሳቸው ቢዋጉም ኢትዮጵያ የሚለው ክብርና ድንበር በሚጣስበት ወቅት አንዱ ባንዱ ላይ ያነሳውን ጦር ይቅር በመባባል በጠላት ላይ አብሮ ይነሳ እንደነበረ የተለያዩ ጸሐፊዎች መዝግበውታል ፤ በህይወትም ያሉም በኩራት በክብር ያወጉናል ።

ኢትዮጵያ ከውጪ የመጣባትን ጠላት ተከላክላ እራሷን ጠብቃ ስትኖር በውስጧ ያለውን የፍትህና ርትዕ ጉድለት ለመቀየር ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማነጽ ግን ፤ በየጊዜው ልጆቿ ጥረት ቢያደርጉም ፤ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ ቅን ሀሳቢዎች ለሕዝብ ተቆርቋሪዎች ዜጎቿ በነበሩትና ባለው መንግሥት ጭምር ተቀጭተዋል ። እንደ ቅጠልም በመርገፍ ላይ ናቸው ፤ ማንኛውም ጸረ ሕዝብና ጸረ ዲሞክራሲ መንግሥት ፍትህ መጓደሉን ፤ ሕዝብን ማሰሩን ፤ መግደሉን ፤ ያገሪቱን ሀብት ያለአግባብ ማባከኑን ከአንድ ሕዝባዊ አስተዳደር የሚጠበቀውን ሀላፊነት ባለመወጣቱ ፤ ሊገርመን ወይንም ከቶውንም ሊደንቀን አይችልም ፤ አይገባም ። ጸረ ሕዝብ ጸረ ዲሞክራሲ ነው ብለን ከፈረጅነው ዘንዳ ፤ ቁም ነገር እንዲሰራ አንጠብቅም ። የአፄ ኃይለሥላሴ ፍጹም ንጉሣዊ መንግሥት የተቃወምነውና ለውድቀትም ያበቃው ከውስጣዊው ባህሪው ተላቆ ሕዝባዊ ሊሆን ባለመቻሉ ነው ። የፋሽስቱ የደርግ መንግሥትም እንደ እንቧይ ካብ በአንድ ጊዜ የተናደው ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ሕዝብ በመሆኑ ፤ ሕዝባዊ ባህሪ ስለሌለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አክ-እንቱፍ ያለው መንግሥት ስለነበረ እንጂ ።

ወያኔም ከፋሽስቱ ደርግ የበለጠ ተጨማሪና አስከፊ ባህሪ ይዞ የመጣው ፤ ጸረ ኢትዮጵያ ፤ ጸረ አንድነት ፤ ፋሽስት ፤ ጠባብ ብሄረተኛና ፤ ዘረኛ መሆኑ ነው ። ከሌሎቹ በጣም የተለየ ያደርገዋል ፤ ሕዝብን መጨፈቅን ብቻ ሳይሆን ፤ አገርን ፤ አንድነትን ማፈራረስ ዋና አላማ አድርጎ የተነሳ ስለሆነ ነው፤ ለዚህም ነው ሕዝባችን በጣም የሚጠላው ፤ የሚቃወመውም ። በአንፃሩ እነዚህን በተለያየ ጊዜ የተከሰቱ ከድጡ ወደ ማጡ የሆኑ መንግሥቶችን ለመታገል በየጊዜው ከግለሰብ ተቃውሞ ፤ እስከ ተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፤ ቡድኖች ድረስ በአንድነት ሆነው የሐገራችንን የውስጥ በሽታ ለማጽዳት የወሰዱት እርምጃና የሕብረት ትግል የሚደነቅ ነው ለማለት አይቻልም ። እንዲያውም ፤ የሕብረት ጉዳይ ሲነሳ አሳፋሪ ነው ብንል ስህተት አይሆንም ።

ያለፉትን ጥፋቶችና ልማቶች ማንሳትና መጣሉ አሁን ላለው ሁኔታ የበለጠ ትምህርት የምናገኝበት ቢሆንም ፤ ይህንን ዘፈኛና ፋሽስት ፤ ጸረ የኢትዮጵያ አንድነት የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ ባለው የሞትና የሽረት ትግል ላይ በተቃዋሚዎች ነን ባዮች ላይ የምናየው የመተባበርና አብሮ የመስራት ጥያቄ ከምን ጊዜውም የበለጠ የሚነሳበት ወቅት ሆኗል ።

ከላይ ፤ ላዩ ሲታይ ሕብረት ስለሚባለው አመለካከትና አመሰራረት ያልገባቸው ፤ አንዳንዶች ደግሞ የግል ሥልጣን ሽሚያ በተቃዋሚዎች መካክል ስላለ ፤ እኔ ልምራ ፤ እኔ

ልምራ በሚል ስለሚጣሉ የሚባል አባባል በሰፊው ይነገራል ፤ ከዚያም በላይ የጠባብና የዘረኛው ፋሽስት የወያኔ አገዛዝ ገንዘብ እየረጨ ፤ አንዱን ካንዱ እያጋጨ ሕብረት እንዳንፈጥር ያደርጋል የሚሉ አስገራሚ ፤ አስቂኝና አሳዛኝ ምክንያቶች ሲሰነዘሩ እንሰማለን ። የምንታገለው አገዛዝ ከከፋፈለን ፤ ከፋፈለን ብሎ ጩኸት ፤ መሳቂያ ብቻ ሳይሆን ይህን ምክንያት አድርጎ ማቅረብ ፤ አስተሳሰባችን ከወያኔ የተሻለ አይደለምና ደካማነታችንን የገልጻል ። ወያኔ መከፋፈል ብቻ አይደለም በግለሰብ ሊያጠፉን ቢችል ያደርገው ነበረ ፤ የተቻለውን እያደረገ ነው ። እያሰረ ከወጣት እስከ ሽማግሌ እየገደለ ያለን አገዛዝ በመከፋፈሉ አንከሰውም ።

ለሕብረቱ አለመሳካት አንዱ ምክንያት የቡድኖች እኔ እበለጥ ፤ እኔ እበልጥ መለስተኛ ምክንያት ሲሆን በሕብረቱም ውስጥ የስልጣን ሽሚያ ስላለ ነው የሚለው ፤ በመጠኑ እውነታ ይኖረው ይሆናል ። ምክንያቱን ዝቅ በለን እናነሳዋለን ።

ሕብረት ለመፍጠር ከዚህ በፊት ብዙ ጥረቶች እንደተደረጉና ፤ በተወሰነም ወቅት ውጤት እንዳሳየ የሚካድ አይደለም ፤ በተለይም የ2005ቱ ምርጫ ፤ ምርጫው ያን ያህል ውጤት ያመጣው በሕብረትና በቅንጅት ስር የተሰባሰቡት ፓርቲዎች ፤ ቡድኖች ባዋቀሩት በድርጅታዊ ስራቸው ውጤት ባይሆንም ፤ እነዚያ አስር አስራ አምስት ድርጅቶች ለየብቻቸው ቢሳተፉ ኖሮ ፤ ወያኔ ሲዘፍንብን ይኖር ነበረ ፤ ምክንያቱም እንደ አንድ ፓርቲ እሱ የበለጠ ድምጽ ማስቀጠሩ አይቀርም ነበርና ። ማበር ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው ። ነገር ግን መሰረት የሌለው ሕብረት የእንቧይ ካብ ነውና ፤ ሕብረትም ቅንጅትም የልደት ዓመታቸውን ሳያከብሩ ፈራረሱ ። እዚህ ላይ ሁለት ነገር እናያለን ፤

- አንደኛ እንደ ድርጅት መጠን ሕዝባዊ መሰረት መኖር አለበት ፤

- ሁለተኛ ሕብረት ለመመስረት የአስተሳሰብ አንድነት በመለስተኛ ደረጃ የፕሮግራም ጥራትን ይጠይቃል ። በዚህ ደረጃ ሕብረት ሆነ ቅንጅት ለትግል ሆነ ለሕብረት በቂ ዝግጅት ያልነበራቸው ፤ ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ ነበርና ፤ ወስከምቢያውን ሲከፍቱት ወጪቱ ተሰባብሯል ። ለዚህ ነው 26 ሚሊዮን ችቦ ይዞ ድምጽ የሰጠውን ሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ የተቸለሰበት ።

2005 ምርጫ በተቃረበበት ሁኔታ የወያኔን አገዛዝ ዲሞክራሲያዊ ለማስመሰል ከነ ጠ/ሚኒስቴር ቶኒ ብሌር የአውሮፓ መንግሥታት እስከ አሜሪካው ቡሽና ከገብሳማው ተቃዋሚ ነኝ ባዩ ድረስ ለመሳተፍና ለማሳተፍ ሲሯሯጡ ወያኔም ከኔ በላይ ዲሞክራቲክ የለም ነገሩ "የረባ ተቃዋሚ" የለም እንጂ ይሳተፉ ብሎ እስኪደነፋ ድረስ ሽር ጉ ተብሏል ። የ2010 ምርጫም እየተቃረበ በመሆኑ በምርጫው ለመሳተፍ ሆነ እንዲሳተፉ ለማዘጋጀት ከውጪ መንግሥታት ፤ ከተቃዋሚ ነን ባዮች ሽር ጉድ ማለቱ ከተጀመረ ወራት አልፏል ።

ባለፉት ወራት የሕብረት ጥያቄ እንደ አዲስ እየተነሳ እየተሰለቀ ነው ። በዚህ አጋጣሚ ስለ 2010 ምርጫ ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ ፤ እንሳተፋለን ለሚሉ ሁሉ ምን ማድረግ አለባቸው? የሚለውን ጥያቄ እስከ ምርጫው ሰዓት ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለማቋረጥ በኢትዮጵያዊን ኃይሎች የጠራ አቋምና አመለካከት እንዲኖር ድርጅቶቹን በሚገባ መሞገትና ተገቢውን ክርክር ማቅረብ አለብን ። ስለ ሕብረትም በምናነሳበት ወቅት ፤ አምና የነበረው የሕብረት መመዘኛ ዘንድሮ እንደማይሰራ መታወቅ አለበት ፤ በአሁኑ ሰዓት የሕብረት መቋቋም መሰረታዊ መመዘኛ ነጥቦችና ፤ በሕብረቱ ውስጥ የሚሳተፉ እነማናቸው? ብለን መጠየቅ የግድ ይሆንብናል ፤ ይህን ጥያቄ ስናነሳ ሁለት አብይ ነጥቦች መልስ ማግኘት አለባቸው ፤

- አንደኛ የወያኔ አገዛዝና ወያኔ ማነው?

- ሁለተኛ የቀድሞ ሕብረቶች ለምን ፈረሱ? የሚለውን በቅጡ ካልተረዳን ፣ ትግላችን ምንድነው? ሕብረቱስ እንዴት ይመሰረታል ለሚለው ጥያቄ ካነሳንና ግልጽ ካልሆንን ስር ነቀል መልስ አያገኝም ። እኛም "ዞሮ ዞሮ ወቅን" ወደ 2005ቱ የሕዝብ ሀዘን እንመለሳለን ፣ አዛኝ ቅቤ አንጓች እንሆናለን ።

ወያኔ ማነው? የወያኔ አገዛዝስ? ወያኔ ማለት የትግሬ ሕዝብ ወኪል ነኝ የሚል ፣ ተጋድሎ ሃርነት ሕዝባዊ ትግራይ የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር (TPLF) በሚል ፣ የትግራይን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ የተጸነሰ ፣ አሁንም በዚያው የሚገፋ የወሮበላና የዘረኛ ጥርቅም የትግሬ ስብስብ ነው ። ወያኔ ለመሆን ወይም የ(TPLF) ድርጅት አባል ለመሆን ፣ አንድ ሰው በግድ ትግሬ መሆን አለበት ። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ከወያኔ ጋር የሰራውን ሁሉ አማራ ፣ ኦሮሞ ፣ ጉራጌ ወዘተ… ወያኔ ሲሉ ይሰማሉ ፣ የተቃወማቸውን ሁሉ ሲያበሻቅጡ ይውላሉ ፣ ለሞሶሎኒ ያገለገለው ሁሉ መንገድ እየመራ አርበኞችን ሲያስመታ የነበረው ባንዳና ሹምባሽ እንጂ ጣሊያን አይባልም ። የኢትዮጵያዊነት ወኔው ሸንቶ ለለት ጥቅሙ ሲል የደለበው ሁሉ ወያኔ ሳይሆን ወያኔ ያኮላሸው ወኔ የሌለው የፖለቲካ ቅጥቅጥ ይባላል ።

ወያኔ ማለት ፣ አንድን ቋንቋ መሰረት በማድረግ ሌላውን ለማጥፋት ፣ አገር ለመበተን ፣ የተሰነሰ ጠባብ ዘረኛ አስተሳሰብ ማለት ነው ። የአማራ ፣ የኦሮሞ ወዘተ… ትግሬ ወያኔ የለውም ፣ አማራ አማራ ነው ፣ ኦሮሞ ኦሮሞ ነው ። የወያኔ አገዛዝ ማለት ለትግራይ ጥቅም ብቻ የቆመ ፣ በኢትዮጵያ መጥፋት ፣ ትግሬን ማልማት በሚል ፍልስፍና ሕገመንግሥቱም (constitution) ኑም በዚህ አንፃር የተሰራ ነው ። በኢትዮጵያ መጥፋት ትግራይን ብቻ ለማሸብረቅ ፣ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የሚያስችለው መዋቅር ነው ወያኔ የሚባለው ። ስለሆነም ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ቋንቋን መሰረት ባደረገ ጠባብ ዘረኛ ቡድን ልትመራ አትችልም ፣ በመሆኑም እውነተኛ ታጋዮች የወያኔን አመራርና ምክር ቤት ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ሕገመንግስቱም ጭምር መገርሰስና መፋቅ አለበት ፣ በምትኩም የኢትዮጵያን አንድነት የሚያረጋግጥ በማንነቷ የማይደራደሩባት ኢትዮጵያ ፣ የሁሉም መሆኗን የሚያስረግጥ ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለ አድልዎ ያለ ገደብ በመንግሥትና ባስተዳደር ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚሳተፉበት የአንድነት መንግሥትና ሕገመንግሥት መተካት አለበት ። ከወያኔ አገዛዝ ጋራ ምንም አይነት ድርድር ሊኖር አይችልም ።

ስለዚህ የሕብረት ጥያቄ ስናነሳ የምንታገለው አገዛዝ መለሰ ዜናዊን ለመቀየርና ሌላ ትግሬ ፣ ወይም አማራ ፣ ወይም ኦሮሞ ፣ ወይም ጉራጌ ለማስቀመጥ ሳይሆን ፣ ወያኔ (TPLF) እና ሕገመንግሥቱን ለማፍረስ መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት ።

ከዚህ በፊት የነበረው ሕብረት ለምን ፈረሰ ? የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት ፣ ቀደም ብለን በጠቆምናቸው ደካማ ምክንያቶች ሳይሆን ፣ በሕብረቱና በቅንጅቱ ውስጥ የነበሩት ፣ ወያኔን ለማስወገድና ለማፍረስ ሳይሆን ፣ ሰላማዊ ኩዴታ ለማድረግ ፣ መለሰን በሌላ ለመቀየር ፣ ሕገመንግሥቱን በመደጓጎም ይዞ ለመቀጠልና ፣ ኢትዮጵያዊ ለማስመሰል ነው ። ይህ ብቻ ሳይሆን አብዛኛዎቹ ከመለሰ ጋር የግል ቅሬታ ያላቸውና በቅርብ አብረው ይሰሩ የነበሩ ናቸው ፣ የወያኔ አገዛዝ ፍልስፍናው ላይ ሳይሆን ከመለሰ ጋር በነበራቸው ጥላቻ እንጂ ። ስለሆነም ነው ሁል ጊዜ ትግላችን ዞሮ ዞሮ ይመለስና የሚጠሩት ሕብረት ወያኔ በራፍ ላይ ቆሞ ወያኔን ለድርድር ማምጣት አለብን በሚል የፈሪ ትግላቸውን የሚደመድሙት ። በዚህ ውስጥ ደግመው ደጋግመው ተዋንያን በመሆን አሁንም ጸረ ወያኔ በመምሰል እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችን በማጥላላትና በማውገዝ ስለ ሕብረት ምስረታ ሲናገሩ እንሰማለን ። ይህ ለመሰባሰብ ሩጫ በሚካሄድበት ወቅት የምናነሳው ፣ የሕብረት የጸረ ወያኔ ትግል የሚቀጥሉትን

ሀሳብ ያዘለ መሆን አለበት ፤ ወያኔና የወያኔን ሕገመንግሥት ማፈራረስ ፤ በኢትዮጵያ አንድነትና ዲሞክራሲያዊ አቋም ላይ የማይደራደሩና ፤ የወያኔን መዋቅር በመሰባበር ፤ የኢትዮጵያን አንድነት ከማይደራደሩ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራት ። ማንኛውም አሁን የሚፈጠሩ ሕብረቶች በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የጠራ አቋም ያላቸው ፤ የወያኔ አገዛዝና መዋቅር ለመሰባበር ለተነሱ ወያኔ ጠላት ነው ባሉ ኃይሎች ብቻ ነው ። ኢትዮጵያን በሕብረትና በአንድነት ሊያቋቁሟት ፤ ሊያቆሟት የአገሪቱንም አንድነት የሕዝቡንም ዲሞክራሲያዊ ነፃነት የሚያስገኙለት እነዚህ ኢትዮጵያውያን ኃይሎች ብቻ ናቸው ።

በአንፃሩ አሁን ሽር ጉድ የሚሉት ፤

- እነ ክፍሉ ታደሰ ፤ የኢትዮጵያ ችግር ኤይድስ ስለሆነ በከፍተኛ ደረጃ መዋጋት አለብን ሲሉ የነበሩ አሁን የግንቦት ፈጣሪ ከወያኔ ጋር በእጅ አዙር ሲዘፍኑ የነበረ ፤
- ብርሃኑ ነጋ ፤ አምና የዲሞክራሲ መንገዱ ትንሽ አባጣ ጎባጣ አለው እንጂ መንገዱ ተከፍቷል ሲለን የነበረ ፤ አንድ ጊዜ ሁለገብ ሌላ ጊዜ በጦር ተመልሶ ቀልዳችሁን አቁሙ የሚል ፤
- አንዳርጋቸው ፤ የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት ፤ ትላንት አማራ ዛሬ ኦሮሞ የሚሆን ፤ ኢትዮጵያን በመቶ ዓመት እድሜ ገድቦ የሚያስቀምጥ ፤
- መስፍን ወ/ማርያም ፤ የድርጅት የትግል ታሪክ የሌለው በገባበት ድርጅት እየሸፈጠ የሚሄድ ፤
- ብርቱካን ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከመቶ በላይ እስረኞች የሉም የምትል ፤
- ሰለሞን ገ/ሥላሴ ፤ እነ ኦነግ ፤ እነ ኦብነግ እያፈሩ ነው እንጂ ኢትዮጵያዊ ናቸው የሚል ፤
- ጌታቸው ፤ ለወያኔ ምርጫ ምስጋና ይገባዋል የሚል ፤
- መርሻ ዮሴፍ ፤ ከኢሕአፓ በለሊት ሸፍጦ የኮበለለ ወያኔጋ ለመግባት አባሎቻችን አነጋግረን እንወስናለን በሎ ቴለቪዥን ያወጀ
- ኦነግ ፤ ሶማሌ ወዘተ… ኢትዮጵያ የምትባል አገር ልትኖርም ላትኖርም ትችላለች የሚል
- የ(TPLF) ኮፒ አረጋዊ ፤ ስዬ ፤ አረና ትግራይ ሁሉም የ (TPLF) አባል የነበሩ አሁንም ጠባቸው ከመለስ ጋር ብቻ የሆነ

እነዚህና የመሳሰሉ ሌሎች በዚህ ጽሁፍ ለማንሳት ብቃት የሌላቸው ባገኙበት ቦታ እንደ ዝንብ ወተት ጥልቅ የሚሉ አያሌዎች አሉ ። እነዚህ ናቸው ሰለ ሕብረት ጥያቄ እያነሱ አሁንም ሕብረት ፈጥረናል የሚሉን ። የሕዝቡ ትግል በተለይም በውጪ ሐገር እንዲዋዥቅ ያደረጉት ፤ አንዳቸውም በግለሰብ ሆነ በቡድን በጠራ መልኩ ወያኔን አይቃወሙም ፤ ሊቃወሙም አይችሉም ። የነሱ ትግልና ሕብረት ግፋ ቢል መለሰን አውርዶ ሰዬ አብረሃምን ከመተካት ያለፈ አይደለም ። የድኅማ ተቃዋሚዎች ከድኅማ ለውጥ አያልፉምና ። ስለሆነም ባሁኑ ሰዓት የምንጠራው ሕብረት ከነዚህ መሰረታዊ እውነታዎች የመነጨና በዚህ የተመዘነ ካልሆነ ነገም እንደ ትላንትናው ትግሉን መጉዳት ብቻ ሳይሆን ፤ ሕዝባችንን ተስፋ ማስቆረጠችን የማይቀር ሃቅ ነው ።
እነዚህን ኃይሎች በርትተን በመተንተን ሕዝባችን እንዲያውቃቸውና ወገናችንን ተገቢውን መሰረታዊ እውነታ ማስተማር የግድ ይላል ። የፖለቲካ ቅጥቅጦችን ጨርሶ በትግሉ ውስጥ ቦታ መንሳት ያስፈልጋል ።

እነሱና እኛ በወያኔ ላይ ያለን ልዩነት የቃላት አተረጓጎም ሾላ በድፍን ጨኸት አይደለም ።

አሁን ሕብረት መሥርተናል የሚሉት የወያኔ ሕገመንግሥት አበጋዞች የነበሩ ናቸውና በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርብናል ።

የብርቱካን ፣ አረና ትግራይ ፣ ግንቦት ፣ አንጃው ፣ ኦነግ ፣ኦብነግና አንዳንድ እነ ሥም አይጠሬ የስደተኛው (Diaspora) አባሎችና ዶክተሮች ከመለሰ ጋር ጠብና ቅሬታ ፣ ተቃውሞ አላቸው ። ይኸውም አብዛኛዎቹ ከመለሰ ጋር ቤተ መንግሥት ውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘው በኢትዮጵያ መጥፋት ላይ ከመለሰ ጋር አብረው በከፈተኛ ስልጣን ሲሰሩ የነበሩ ፣ በተወሰነ ወቅት በጥቅም ተጋጭተው የሸሹ ፣ አሁንም ያ የበሉት የደም ወጭት እየጠራቸው ከመለሰ ጋር በአንድ ጠረጴዛ እንደራደር የሚሉ ናቸው እንጂ በሥራቱ ችግር የላቸውም ።

የመኢሶን ድርጅት ከፅንሱ የዚህ ዓይነት አመለካከት ስለነበረው ያስከተለውን ጉዳት ማየት ይጠቅማል ፣ በዶክተር ኃይሌ ፊዳና በዶክተር ነገደ ጎበዜ ይመራ የነበረ ይህ ድርጅት ከመሰረቱ ሲፈጠር የወታደሩን መንግሥት እያስተማሩ አብሮ በመስራት መለወጥ ፣ ሥልጣን መያዝ ፣ ኢትዮጵያንም መገንባት ይቻላል የሚል የተበረዘ ፍልስፍናቸውን ይዘው ከደርግ ጋር በመጠጋት ፣ በዚያም ሌሎች እነ ሰናይ ልኬ ኢጭአት ይህን አይነት ሀሳብ በማቀንቀን የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን ፍቅርና ተቀባይነት ለማግኘት ሲፏከቱ ሁሉም አልቀው ፣ አገሪቱም ማጥና ውድቀት ውስጥ እንድትገባ አድርገው ይኸው ከሁሉም ለወሬ ነጋሪ ከመኢሶን ዶክተር ነገደ ጎበዜ ብቻቸውን ቀርተዋል ። ከታሪክ አለመማር አሁንም ስለሕብረት የሚሰልቁልን ከነመለሰ ጋር በመደራደር ገብቶ መለወጥና ማሻሻል ከዚያም መለሰን መግፋት ይቻላል በማለት የነመኢሶንን ታሪክ ሊደግሙ ይዳዳቸዋል ።

መኢሶኖችና መሰሎቻቸው ደርግን በሚገባ አሰልጥነውታል ፣ መርህ አስጨብጠውታል ፣ ድርጅት እንዴት እንደሚፈጠር ፣ እንዴት እንደሚዋቀር አሳይተውታል ፣ ከቀበሌ ማሕበር እስከ ገበሬ ማሕበር ፣ ከነበልባል እስከ ኢሰፓ ፣ እንዲመሰርት አስተምረውታል ። በመጨረሻም አገሪቱንም አጥፍቶ ፣ የፈጠሩትንም ድርጅትና እራሳቸውንም ደምስሶ ፣ በመጨረሻም ሁሉም ለጥፋት የተዳረጉ ነበሩና በኢትዮጵያ ታሪክ በጥቁር መዝገብ ይኖራሉ ።

የአሁኖቹም ሕብረት ፈጣሪዎች ከነአንዳርጋቸው እስከ ብርሃኑ ነጋ ፣ ከነብርቱካን እስከነ ስዬ ፣ አረና ትግራይ ፣ ኦነግ ሁሉም ከነመለሰ ጋር አብረው ሲያስተምሩ ፣ ሲማሩ ፣ ሲያጠፉ ፣ አገር ሲገሉ የነበሩ ፣ ዛሬ በመውጣታቸው (የአንዳንዶች አወጣጥ አጠያያቂ ቢሆንም) ወይም እስር ላይ በመቆየታቸው የወያኔን ስርአትና አገዛዝ ጨርሶ ለመደምሰስ የተነሱ በመምሰል የወያኔው መሪ መለሰን መቃወም ወያኔን እንደመቃወም አድርገው ያቀርቡታል ። አይደለም ።

ከኛ ጋር ያለን ልዩነት ግልጽና ብሩህ ነው ፣ መለሰ ይውጣ ሲሉ ፣ የወያኔ ሥርአት ይፍረስ ፣ "ይገርሰስ ከሀገራችን ምድር ይፋቅ " ብለን ነው የምንታገለው ። ሕገመንግሥቱ ይፍረስ ፣ የጸጥታ መዋቅሩ ይበጣጠስ ፣ አስተዳደሩ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀፈ መሆን አለበት ስንል ፣ እነ ግንቦቴና አንድነት ፣ አንጃው ፣ አረናው ፣ ሁሉም የለም ቀስ ብለን ከመለሰ ጋር በአንድ ጠረጴዛ ተደራድረን የምናሻሽለው ይሆናል ይሉናል ። ስለሆነም በሁለታችን የትግል ጎዳና ያለው ልዩነት መሰረታዊ ይሆናል ።

ትግላችንም የመረረና የከፋ እንዲሆን ያደረገው የነዚህ ቅጥቅጥ ፖለቲካ ፣ በነ መኢሶን ተፈትኖ ለእልቂት ያበቃን ፍልስፍና አሁንም ያለንን ኃይል እንዳይሰባሰብ አድርጎታል ። ይህን ሃቅ አበክረን ማየት አለብን ።

ስለሆነም ዋነኛው ጠላታችን የወያኔ ስርአት ሕገመንግሥቱና አስተዳደሩ ፤ የጸጥታው ወዘተ... መሰባበር ነው ። በኛና በነሱ መካከል ያለው ልዩነት በግርድፉ ይህ ነው ። ስለ ሕብረትም ሆነ ሰለ ምርጫ 2010 ስናነሳ ልዩነታችን በዚህ ይፈረጃል ።

በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ሐገር ፤ ሕበረት ፈጠርን የሚሉት እነማን ናቸው? ግንኙነታቸውስ? ብለን እንጠይቅ ።

በውጭ አገር የሚገኙት ተቃዋሚ ነን ባዮች ካወጡት መግለጫ

- የአንድነት ድጋፍ ሰጭ በሰሜን አመሪካ
- የአንድነት ድጋፍ ሰጭ በካናዳ
- የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ዴሞክራቲክ (አንጃው)
- የግንቦት ንቅናቄ
- ጋሻ ኢትዮጵያ
- የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባኤ
- የኢትዮጵያ ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ ናቸው ።

በሐግር ቤት ደግሞ ፤-

- የአንድነት ፓርቲ (ብርቱካን)
- አንድነት ፤ አረና ትግራይ ፤ ሶዴኃቅ ፤ ኦፌዴን ፤ ኦብኮ ፤ ስዬ አብርሃ ፤ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ፤ ወዘተ...

እነዚህ የተነጣጠሉ እራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶች ናቸውን? ወይስ በባህሪያቸው ፤ በይዘታቸው እንደ ሸረሪት ድር ተጠላልፈው የተዘረጉ ድርና ማግ በመሆናቸው እነማናችሁ? ታሪካችሁስ ምንድነው? ብለን መጠየቅ መብታችን ብቻ ሳይሆን ሐገራዊና ፤ ኢትዮጵያዊ ግዴታችን ነው ።

ያለፈው ተሞክሯችን አስተምሮናልና የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ በሰሜን አሜሪካ ፤ ቅንጅት በአውሮፓ ፤ የቅንጅት ድጋፍ በካናዳ ፤ እየተባለ የውጭ ውክልናው ላይ አሸሸ ገዳሜ ሲሉ የነበሩትን ፤ የነ ብርሃነ መዋና የነ አንዳርጋቸው ጽጌን ታሪክ አንዘነጋውም ። የነ አረጋዊ መለሰን ወይንም ወያኔን ተቃውሞ ለቅንጅት ያላቸው ድጋፍና አክብሮት ሌላው ሌላውም ወከባና ማደናበር ሁሉ እንደዚያው ነው ።

እናም ብርቱካን ባገር ቤቱ መድረክ ፤ የድጋፍ ሰጪው አካል ደግሞ የውጭ አገር ያለው ሕብረት አካል ፤ ስዬ ያገር በቱ አባል ፤ አረጋዊ ደግሞ የውጭ አገሩ ሕብረት አባል ፤ እነ አንጃው በውጭ አገር ፤ እነ በየነ ጴትሮስ በፓርላማ ፤ ስለዚህ ዞሮ ዞሮ የሐገር ቤቱ መድረክና የውጪው አገር ሕብረት የተቆላለፈና የተቆራኘ ነው ማለት ነው ፤ ላላስተዋለና አሰራራቸውን ላርመረመረ ግን ቃላቸውን ብቻ ተቀብሎ የውጪው ሕብረትና ያገር ቤቱ መድረክ ግንኙነት የሌላቸው ለማስመሰል ጥረት ሲደረግ ይስተዋላል ።

እንደኛ ሁሉም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሳይሆኑ ፤ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ (sub committee) ናቸው ። የወያኔ (TPLF) ተዋረድ አቀንቃኝ ናቸው ። መድረክም ሆነ የውጪው ሕብረት አብረው እንዲቀናጁ በአበው አነጋገር "ይቅር ለምንት እግዚአብሄር" እንባባል ነው ። በፖለቲካ ደግሞ "ተቃዋሚ" እንባልና እንተባበር ይባላል ፤ ይህ ነው ተቃዋሚ ፤ ይህ ነው

ሕብረት ፤ ይህ ነው መድረክ ፤ የወያኔ እጅ ከአገር ቤት እስከ ባህር ማዶ የተዘረጋበት መስመር ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደንቆሮ ነው ብለው ከመገመት የተነሳ ነው የሚሰሩትና የሚናገሩት ። አሰራራቸው ከአንድ ክምር ገለባ የቀለለ ብቻ ሳይሆን ፤ መለሰ በተቆጣ ቁጥር እሱን ለማስደሰት ፤ የሱፍ አበባ ፀሀይን እየተከተለ አንገቱ እንደሚደፋ ሁሉ የሱን ፈገግታና ቡራኬ የሚያዩበት መንገድ ሲፈልጉ አንገታቸውን እንደደፉ ይኖራሉ ።

ለይስሙላ ታጋይ መምሰል አይቻልም ። ለይስሙላ እስር ቤት መግባትም ታጋይ አያደርግም ፤ አርበኞችን ሊሆኑ አይችሉም ። እንደሚባለው ሌባም አብዮተኛ ፤ ነጻ አውጪ በተባለ ነበር ። በመስረቁ ፤ በመታሰሩ ፤ በመፈታቱ ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ የሚሰርቀውና የሚታሰረው ለራሱ ለግል ልክስክስ ጥቅም ከመሆኑም በላይ የሚሰርቀውን ሰውና ቤት ስለማይለይ ወገን አሳፋሪ ተብሎ ከዘመድ አዝማድ ይገለላል ፤ በሽማግሌም ፤ በቄስ ቢመከር ተመልሶ መልከስከሱ አይቀርም "ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም" እንደሚባለው ።

የኛ ተቃዋሚ ነን ባዮች 2005 ላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባዶ ሜዳ ላይ ለመለሰና ጅቦቹ ጎልተውት እንደሄዱ ዘንግተውታል ። በ2005 ም በየድርጅቱ ተሰግስገው ከነ በረከት ስሞኦን ትእዛዝ እየተቀበሉ ይፈጽሙና ያስፈጽሙ እንደነበረ ፤ በዚያን ወቅት የገዛ ጓደኞቻቸውን የውስጥ አርበኛ ሆነው በመጠቆም ያሳሰሩና የሕዝብን ማዕበልና ሰላማዊ ሰልፍ እንዳልበተኑ ሁሉ ፤ ሕዝብንም እንዳላስጨረሱ ሁሉ አሁን ሰላማዊ ትግል ጠሪ ፤ በሕብረት ታጋይ ፤ በመድረክ ዘፋኝ ፤ ሆነው ሲመጡ ፈሪሃ እግዚአብሄር ይደርባችሁ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለቀቅ አድርጉት ማለት ቀደም ብለን ለጠቀስነው ተራ ሌባ ያገር ሽማግሌ ከሚመክረው ያላነሰ ተመጣጣኝ ምክር ይሆናል ። "ቢተው ይተው ፤ ባይተው ወዳጅ ይምከረው ፤ ጀምበር በሰረቀ ሁልጊዜ አፈርሳታ" የተባለው " ቢተው ፤ ጅንበሬና ወዳጅ" የተባሉ አገር ያሰለቹ ሌቦች በፈጠሩት ችግር የተነሳ ሽማግሌ በዘዴ ሌቦችን ለማጋለጥ ያሉት አባባል ነው ። እኛም የምንለው የትኛው ቢተው ፤ የትኛው ጀምበር ፤ የትኛው ወዳጅ እንደሆነ ለመለየት ጊዜ ባናጠፋም ፤ በአጠቃላይ ለኛም ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሰልችታችሁታል ፤ ምርጫ በመጣ ቁጥር አተላ እንዳየ በሬ አትቅነዝነዙ እንላለን ።

ሕብረት ለመመስረት ሕዝባዊነት ይጠይቃል ፤ ሕዝባዊ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አክ-እንቱፍ ብሎ የተፋውን የፋሽስቱና የዘረኛውን የወያኔን አገዛዝ ጠላት ማለትና መዋጋትን ይጠይቃል ፤ ሕብረት ለመመስረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያዊነትን መቀበልን ያሻል ፤ ኢትዮጵያዊነትን ለመቀበል ደግሞ ከሁሉም በፊት ኢትዮጵያ የማትነጣጠል አንድ አገር መሆኗን ማመንና መቀበልን የግድ ይላል ። ሕብረት ለመመስረት የራስን ምቾት ተወት አድርጎ የሕዝቡን መከራ ፤ ስቃይ ፤ የመብት መገፈፍን ፤ የሰባዊ መብቱ መረገጥን ፤ የተፈጥሮ ጸጋውን ማጣት ፤ ዲሞክራሲያዊ መብቱን መነፈግ ፤ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነጻነቱ መገፈፉን መገንዘብ ይጠይቃል ። እነዚህን ሃቆች ለመገንዘብ የሕዝቡ ነጻነትና አንድነትን ለማግኘት የወያኔን አገዛዝ ከስር ተነቅሎ እንዲፈርስ በማንኛውም የትግል ዘዴ ለመታገል መነሳትን ፤ የወያኔን አገዛዝ የ(TPLF) ድርጅት ጠላትነቱን አውጆ ቆርጦ ከወያኔ ጋር የተሳሰረን እትብት መቁረጥ ያስፈልጋል ። ይህን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያዊነት ወገን መሆንን ባማያሻም ማስቀመጥ ይኖራል ፤ ይህ ሕዝባዊ ቅንነት እራስን ለሕዝብ ታማኝ አድርጎ ከመቅረብ የሚመነጭ ነው ።

ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጾመኛ ነኝ ማለት ፤ በአርባ ጾም ደመና ሆቴል ገብቶ ሽፍንፍን ማዘዝ ነው ። አለበለዚያ ጥርሱን አውልቆ የጨረሰ ወላቃ ነኝ ላለማለት በጾም ምክንያት ሥጋ ማኘክ አለመቻሉ እንዳይታወቅበት የሚተርከው ታሪክ ነው ።

"ወያኔን ተዉልኝ ፤ መለሰን አውጡልኝ" ከጠቀስነው ተረት የተወለዱ ዜጎች ካልሆኑ በስተቀር ፤ ሕብረት መሥራች ሊሆኑ አይችሉም ። የማይናከስ ጥርሱ ያለቀበት ውሻ ቤት አይጠብቅምና ። መጮህ ብቻ ተቃዋሚ አያደርጋችሁም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕብረት አላችሁ ወይንም መድረክ አላችሁ ብሎ አይነዳም ፤ በቀን ያሰራችሁትን ማተብ በሌሊት እንደምታፈርሱ ከ2005 ታላቅ ትምህርት ተምሯል ።

2010 ሩቅ አይደለም ፤ ማንም ኢትዮጵያዊ በወያኔ ላይ የጠራ አቋም የሌለው ፤ ወያኔን በጠላትነት ያልፈረጀ ፤ ቀንደኛ ጠላቱ ወያኔ መሆኑን ያላስረገጠ ፤ የፖለቲካ ለማጣ መሆን ብቻ አይደለም ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የሚነግድ የፖለቲካ ቸርቻሪ ሱቅ በደረቴ ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫው ጊዜ እንዳይወጣ ፤ እንዳይመርጥ ማስረዳትና መቀስቀስ የኛ ታጋዮች ግዴታ ነው ።

የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቀው ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ድርጅቶች፤ የሚያነሷቸው ደረቅ ሃቆችን የተመረኮዘ ስለሚሆን ፤ ሕብረታቸውም የጸና በደም የተገነባ ይሆናል ። እነዚህ ኃይሎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው ለዘላቂው ትግል አስተማማኝ የትግል ጓዶች ሆነው የሚዘልቁት ። እነዚህ ኃይሎች ናቸው መሪ ድርጅት ሆነው የሽግግር መንግሥት ይሁን ሌላ ሁሉንም አቀፍ መንግሥት ለማቋቋም ኢትዮጵያንም የጸዳችና የሁሉም ሕዝብ እኩል ዴሞክራሲያዊ ሐገር የምትሆነው ። በዚህ አይነት መተክል ባለው የተባበሩ ድርጅቶች ብቻ ናቸው ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ፤ አንድ ኢትዮጵያን የሚያንጸባርቅ ሕገመንግሥትና አስተዳደር ሊፈጠር የሚችለው ።

የወያኔን አገዛዝ ለመታገል የኢትዮጵያን ሕዝብ በዚህ ትግል ውስጥ ለማሳተፍ ፤ ብሎም የአግሪቱን አንድነት ለመጠበቅና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማቋቋም ሀቀኛ ድርጅቶች ፤ አገር ወዳዶች ፤ የተለያዩ የሲቪክ ማህበራት ከላይ በጠቀስናቸው መርሆዎች መሰረት መሰባሰብና ለዘላቂው ትግል ዘላቂ ሕብረት መፈጠር ይችላሉ ። አንዳንድ ባለውና በተከሰተው የሕብረት አመሰራረትና አወዳደቅ ምክንያት ብዙ ታጋይ ኢትዮጵያዊ በሕብረት አፈጣጠርና መፈጠር ላይ ተስፋ መቁረጡ አያስገርምም ፤ ነገር ግን እንዲህ አይነት ክስተት በማንኛውም የትግል ወቅት ላይ የሚከሰት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ። በትግሉ ውስጥ የውጣ ውረዱ አንዱ አካል ነውና ። ከዚህ ክስተት በመነሳት በትግላችን ውስጥ ሕብረት መፍጠር አይቻልም የሚል አስተሳሰብ ፍጹም ስህተት ይሆናል ። አምና ውኾንብር ውስጥ የነበረው ትግላችን እንክርዳዱ ከስንዴው ሲለይና ባንድ ወገን ተበጥሮ ሲወጣ ዘንድሮ እንዳየነው ትግላችን አንድ እርምጃ ወደፊት ሄዷል ። ይህ ሁኔታ የጠሩ ታጋዮችና ድርጅቶች የከረረ ክንዳቸውን በወያኔ አገዛዝ ላይ እንዲያነሱ ውስጣዊ ጥንካሬን ሰጥቷቸዋል ።ይህም ጥንካሬ እንዲቀጥል መሰረቱም እንዲሰፋ ማንኛችንም እውነተኛ ሕብረት እንዲቋቋም ከምን ጊዜውም የበለጠ መስራት ይኖርብናል ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ይሄንን ከኛ ይጠብቃል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያቸንፋል !!